# የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ።

## ምዕራፍ ፡ ፺፫ ።

የንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዕረፍት ፤—የግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ተፈሪ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነት ፡ ዘውድ ፡ መድፋት ።

ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ባባታቸው ፡ ዙፋን ፡ ባ፲፱፻፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ መስከረም ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ተቀምጠው ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ «ንግሥተ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ወለቱ ፡ ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ» ፡ እየተባሉ ፡ በደግነትና ፡ በርኅራኄ ፡ ፲፫ ፡ ዓመት ፡ ከ፯ ፡ ወር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሲገዙ ፡ በመጨረሻ ፡ ሕመም ፡ አድሮባቸው ፡ ነበርና ፡ በመጋቢት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ዐርፈው ፡ በታላቅ ፡ ሐዘንና ፡ ፍታት ፡ ባባታቸው ፡ መቃብር ፡ በመታሰቢያ ፡ ቤት ፡ ተቀበሩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ተፈሪ ፡ «ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥዩመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ» ተብለው ፡ መንግሥትን ፡ ያዙ ።

የዘውዱም ፡ በዓል ፡ እንዲከበር ፡ የተወሰነው ፡ ንግሥት ፡ ካረፉ ፡ በኋላ ፡ በ፯ኛው ፡ ወር ፡ በጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ነበርና ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ አክባሪ ፡ ለመሆን ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገኝ ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አኳኋን ፡ ሲያጌጥና ፡ እንዲሁም ፡ ለበዓሉ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደሚገባው ፡ ሲዘጋጅ ፡ ቈየ ።

በዚህም ፡ በዘውዱ ፡ በዓል ፡ ምክንያት ፡ ከሚገኘው ፡ ደስታ ፡ ተሳታፊ ፡ ለመሆን ፡ ከዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ውስጥ ፡ የታወቁት ፡ እንደራሴዎቻቸውን ፡ ልከው ፡ ነበር ።

የመጡትም ፡ ዝርዝራቸው፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

፩ ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ልዑል ፡ ሔንሪ ፡ የግሎስተር ፡ መስፍን ።

፪ ፡ ከአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ክቡር ፡ ሀ ፡ መሪ ፡ ጀኮፔ ።





የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ።

